# ደንብ

## የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS

| | |
|---|---|
| **ተዛማጅ ሠነዶች:-** | ABA-RB፣COB-RA፣DJA-RB፣EBH-RA፣EGF-RB፣EIB-RA፣EKA-RA፣ IGK፣KGA-RA |
| **ኃላፊነት የሚመለከታቸው ጽ/ቤቶች:** | የአካዳሚክ ዋና ኦፊሰር ቢሮ፤ የስርዓት አቀፍ ደህንነት እና የድንገተኛ አደጋ ማኔጅመንት ቢሮ፣ የትምህርት ቤቶች ድጋፍ እና ደህንነት ቢሮ |

# በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ንብረት ላይ ትናንሽ የሰው አልባ አውሮፕላን ሲስተሞችን (ድሮኖችን) ማብረር

## I. ዓላማ

በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ንብረት ላይ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ሰራተኞች እና ተማሪዎች ፈቃድ ባለው የድሮን ኦፐሬተር አማካይነት ቀጥተኛ ቁጥጥር እየተደረገ ሰው አልባ አውሮፕላኖችን (UAS) (ከዚህ በኋላ "ድሮን" እየተባለ የሚጠራው) ለትምህርት ዓላማ የአጠቃቀም መመሪያ እና ሂደቶችን መመሥረት።

ሌሎች ለመዝናኛ ተጠቃሚዎች በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ንብረት ላይ ማንኛውም መጠን ያላቸው ድሮኖችን ማብረር የተከለከለ መሆኑን ለመደንገግ።

## II. ዳራ

የፌዴራል ህግ እና የፌደራል አቪዬሽን አስተዳደር (FAA) ስለ ድሮኖች አጠቃቀም በሚመለከት እንዴት እንደሚፈቀድ መመሪያ ደንግገዋል። ስለ FAA ደንብ በተሳካ ሁኔታ ዕውቀት ላላቸው የሰው አልባ ድሮን ኦፕሬተሮች FAA ሠርተፊኬት ይሰጣቸዋል። በ FAA ደንብ ላይ ካሉት መስፈርቶች መካከል የተወሰነ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ንብረቶችን የሚያካትት የተገደበ የአየር ክልል ይገኝበታል። FAA ደንብ ላይ በተደነገገው መሠረት ማንም ሰው ከሚመለከተው ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ ቅድሚያ ፈቃድ ካልተሰጠው በስተቀር በተከለከሉ ወይም ጥብቅ ቁጥጥር በሚደረግባቸው አካባቢዎች ላይ ሰው አልባ ድሮን ማብረር (ኦፐሬት ማድረግ) እንደማይችል ያረጋግጣል።

## III. ትርጉም

A. በዚህ ደንብ አገላለጽ ድሮንUAS ማለት፣FAA እንደገለጸው በድሮን ኦፕሬተር አማካይነት በአሜሪካ የአየር ክልል ውስጥ በአስተማማኝ እና በብቃት ኦፐሬት የሚደረግ ከ 250 ግራም በላይ እና ከ 55 ፓውንድ በታች የሆነ በራሪ ሰው አልባ ድሮን[1] እና ተያያዥ አካላቶቹን (የግንኙነት መሣርያዎቹ እና ሰው አልባውን ድሮን መቆጣጠርያ ክፍሎቹን) የሚያጠቃልል በራሪ ድሮን ነው።

[1] የሰው አልባ አውሮፕላን ሲስተሞችን (UAS) ወይም ከ 55 ፓውንድ በታች ክብደት ያላቸው ድሮኖችን በብሔራዊ የአየር ክልል ሲስተም (NAS) ኦፐሬት የማድረግ ደንብ 14 CFR ክፍል 107 ሲሆን ይኼውም ትንሹ UAS ደንብ ተብሎ ይታወቃል።

B. የድሮን ኦፐሬተር ማለት በ FAA ትንሹ UAS ህግ (ክፍል 107) መሠረት አስፈላጊውን የ FAA ፈተና በተሳካ ሁኔታ ማጠናቀቁን የሚገልፅ ወቅታዊ FAA የሪሞት ፓይለት ሰርተፍኬት ያለው/ያላት ግለሰብ ነው።

C. ድሮን የሚፈጥረው ክስተት[2] ማለት –

1. በድሮን ኦፐሬሽን ምክንያት በንብረት ላይ የሚደርስ ጉዳት ወይም የድሮን ጉዳት እና/ወይም

2. ድሮንን መልሶ ማግኘት –

a) ከ MCPS ንብረት ውጭ፣ሌላ የህዝብ ንብረት ላይ፣ወይም ከንብረቱ ባለቤት ፈቃድ ማግኘት የሚያስፈልገው የግል ንብረት ውስጥ ድሮኑን ፈልጎ ማግኘት ወይም

b) እርዳታ የሚያስፈልገው ማንኛውም ፍለጋ። ተማሪዎች እና ሰራተኞች ድሮን ለመፈለግና ለማግኘት ብለው አውራ መንገድ ላይ መውጣት፣ ጣራ ላይ መውጣት፣ ወይም ሽቅብ መንጠላጠል የለባቸውም።

D. የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ንብረት ማለት ማንኛውም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ትምህርት ቤት ወይም ሌላ ተቋም፣ ንብረትነቱ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የሆነ የመጫወቻ ሜዳ ወይም የሚተዳደር ሌላ መገልገያ፣ወይም የ MCPS አውቶቡሶች፣ እና ሌሎች የ MCPS ተሽከርካሪዎች እና ፋሲሊቲ እና/ወይም ተማሪዎችን የሚያካትቱ ማናቸውም በ MCPS የሚካሄዱ እንቅስቃሴዎችን ያጠቃልላል።

E. የጣቢያ አስተዳዳሪ/ተወካይ ማለት ባለቤትነቱ የ MCPS የሆነ ፋሲሊቲ የት/ቤት ርእሰመምህር ወይም ተወካይ ማለት ነው። የጣቢያው አስተዳዳሪ/ተወካይ ለድሮን በረራ ፈቃድ ከሰጠ(ች)፣ በረራው በሚከናወንበት ወቅት MCPS ንብረት ላይ መገኘት አለበ(ባ)ት ወይም በሆነ ምክንያት ንብረቱ ካለበት ቦታ ለቀው መሄድ ካለባቸው በቦታው ላይ ተተኪ የሚሆን ሰው እንዲቆይ ያደርጋል/ታደርጋለች።

F. የጣቢያ ስፖንሰር ማለት ሰው አልባ ድሮን በረራ ለማድረግ ጥያቄ ያቀረበ(ች)፣ጥያቄው እንዲፀድቅ የሚያስተባብር እና በድሮን በረራ ላይ የሚሳተፉ ተማሪዎችን የሚቆጣጠር/የምትቆጣጠር የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኛ ነው(ች)።

a) የድሮን ኦፐሬተሩ(ሯ) እንግዳ አቅራቢ ከሆነ(ች)፣ የጣቢያው ስፖንሰር አድራጊ በድሮን በረራ ውስጥ የሚሳተፈው ክፍል መምህር ሊሆን ይችላል/ልትሆን ትችላለች። በዚህ ዓይነት ሁኔታ መምህሩ(ሯ) በቦታው ላይ ለሚገኘው/ለምትገኘው የድሮን ኦፐሬተር ሀላፊነት አለው።

b) የድሮን ኦፐሬተሩ የሚያስተምረው ክፍል በድሮን በረራ ላይ የሚሣተፉ የ MCPS መምህር ከሆነ(ች)፣የሰው አልባ ድሮን በረራ ለማካሄድ ጥያቄውን ለማቅረብ እና አስፈላጊውን ፍቃድ ሊያስተባብር ይችላል፣ነገር ግን የተማሪዎቹን ተሳ ለመቆጣጠር ሌላ የ MCPS ሰራተኛ በቦታው መገኘት አለበት።

---

አንዳንድ የስጋት ደረጃዎች፣ የሚያደርሰው ጉዳት፣ ወይም በሰራተኞች ወይም በተማሪዎች ላይ ስለሚደርስ ጉዳት፣ወይም የትምህርት ቤት ስራዎችን በእጅጉ የሚያውኩ ክስተቶችን ለመገንዘብ [2] MCPS ደንብ COB-RA፣ ያጋጠመ ክስተትን ሪፖርት ማድረግየሚለውን በተጨማሪ ይመልከቱ።

G. ተማሪ ኦፕሬተር ማለት፡ሰው አልባ ድሮን ለማብረር ከ FAA ሠርተፊኬት የሌለው/የሌላት እና ሰው አልባ ድሮኖችን ለማብረር FAA ሠርተፊኬት ባለው ኦፕሬተር ቀጥተኛ ቁጥጥር እየተደረገ ድሮን የሚያበር የ MCPS ተማሪ ወይም ሰራተኛ ነው።

## IV. *መመሪያ*

A. የሚፈቀድ የድሮን አጠቃቀም

1. የስርአተ ትምህርት እና የማስተማር ፕሮግራሞች ቢሮ (OCIP) ሳይንስ፣ቴክኖሎጂ፣ኢንጂነሪንግ፣ ሂሳብ (STEM)፣ እና የአቪዬሽን ከሪኩለም፣ የመሳሰሉትን ለማስተማሪያነት ድሮን መጠቀም የሚያስፈልጉ የ MCPS ትምህርታዊ ፕሮግራሞችን በግልፅ መስቀመጥ ይችላል።

2. የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች እና ሰራተኞች ሰው አልባ አውሮፕላኖችን መጠቀም የሚችሉት በ MCPS ንብረት ላይ በ FAA የተረጋገጠ ሰው አልባ አውሮፕላኖችን ኦፕሬት ለማድረግ ሰርተፊኬት ባለው ሰው ቁጥጥር ስር እና በተፈቀደ የበረራ እቅድ መሰረት ነው (ክፍል V.B.1-2 ይመልከቱ)።

3. የሚከተሉት አይፈቀዱም፡-

    a) ከመደበኛ ትምህርት ውጭ ድሮኖችን መጠቀም በአጠቃላይ ተቀባይነት አይኖረውም።

    b) በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ንብረት ላይ የመዝናኛ ድሮኖች እና ሞዴል አውሮፕላኖች አይፈቀድም (በተጨማሪ MCPS ደንብ KGA-RA በህዝብ ትምህርት ቤቶች የማህበረሰብ አጠቃቀም እና የሞንትጎመሪ ካውንቲ የህዝብ መገልገያዎች የማህበረሰብ አጠቃቀም ቢሮ (CUPF)የፋሲሊቲ አጠቃቀም ፍቃድና ስምምነት)ይመልከቱ።

    c) FAA ደንብ ላይ እንደተደነገገው FAA በገለጸው መሠረት "Class B, Class C, Class D, and Class E" የተከለከለ የአየር ክልል ውስጥ በሚገኙ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ንብረቶች ላይ ከቤት ውጭ የሚደረጉ የድሮን በረራዎች አይፈቀዱም።

    d) በሌሎች የውጪ የቡድን እንቅስቃሴዎች በሚካሄዱባቸው ሥፍራዎች አካባቢ በረራ አይፈቀድም (ለምሳሌ፡- የስፖርት ዝግጅቶች/ልምምዶች ወይም ስፖርታዊ ትምህርት በሚሰጥባቸው አካባቢዎች) አጠገብ አይፈቀድም።

    e) ተማሪዎችን የሚያሳትፉ የድሮን በረራዎች ላይደረጉ ይችላሉ –

        (1) ከሰዎች አናት ከፍ ብሎ ወይም ከተሽከርካሪዎች ከፍ ብሎ፣ ወይም

        (2) በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ንብረት ላይ በሚገኙ ትምህርት ቤቶች፣ ስታዲየሞች፣ ወይም ሌሎች መዋቅሮች አጠገብ ወይም ከፍ ብሎ በረራ ማድረግ።

(3) ከሥራ ጋር በተያያዘ ምክንያት ከላይ መብረር የሚቻለው (1) ወይም (2) (ለምሳሌ፦ የግንባታ ሥራ ወይም የአውቶቡስ መናኸሪያ ዴፖዎችን ለመቆጣጠር) በኦፕሬሽን ዋና ኦፊሰር/በተወካዩ ሲፈቀድ ነው።

B. (ለማስተማሪያ) የበረራ መስፈርቶች

1. ተገቢ የተማሪዎች ቁጥጥር ከማድረግ አንጻር (ክፍል III.F ይመልከቱ) ፈቃድ ያለው/ያላት የድሮን ኦፕሬተር (ክፍል V.B.1 ይመልከቱ) እና የጣቢያው ስፖንሰር መገኘት አለባቸው። "መገኘት" ማለት የድሮን ኦፕሬተሩ በረራውን ለመቆጣጠር በሚያስችል ክልል ውስጥ መገኘት ሲሆን MCPS ንብረት ላይ መገኘት ያለበት የጣቢያው አስተዳዳሪ ነው።

2. በማንኛውም የበረራ ወቅት፣ሰው አልባ ድሮኑ—

   a) ለድሮን ኦፕሬተር በሚታይ ሁኔታ፣

   b) ከ 400 ጫማ በታች እና በበረራ እቅዱ ላይ በተጠቀሰው የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ንብረት ክልል ውስጥ መሆን ይኖርበታል።

3. ኦፕሬተሮች/ተሳታፊዎች

   a) ምንም እንኳን ድሮኖቹ የሚበሩት ከሌሎች በተለይ በተወሰነ አካባቢ (ማለትም፦ በተወሰነ ክልል) ቢሆንም ሁሉም ኦፕሬተሮች/ተሳታፊዎች የደህንነት መነጽር ማድረግ አለባቸው።

   b) ተማሪ የድሮን ኦፕሬተሮች FAA የተረጋገጠ የሪሞት ፓይለት መስፈርቶችን እና ይህንን ደንብ መረዳታቸውን ለማረጋገጥ በአስተማሪያቸው የተሰጣቸውን ፈተና በተሳካ ሁኔታ ሲያጠናቅቁ መቆጣጠሪያዎቹን ኦፕሬት ማድረግ የሚችሉት በመምህራቸው ፈቃድ ብቻ ነው።

4. የድሮን አጠቃቀም ዝርዝር መግለጫ

   a) መቆጣጠሪያዎቹ ሲለቀቁ የሚያንዣብቡ ሰው አልባ ድሮኖች ብቻ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ንብረት ላይ እንዲበሩ ይፈቀድላቸዋል።

   b) በአምራች ኢንዱስትሪው ያልተፈቀዱ/ያልተመረቱ ሌላ ሞደፊክ መለዋወጫ የተቀየረላቸው ሰው አልባ ድሮኖችን ማብረር የተከለከለ ነው።

## V. ፍቃድ መስጠት፣ ሪከርድ መያዝ፣ እና ክስተትን ሪፖርት የማድረግ ሂደቶች

A. ኃላፊነት የሚመለከታቸው ቢሮዎች

1. OCIP ፋውንዴሽን ቢሮ የበረራ እቅድ ማመልከቻዎችን የመገምገም እና ፈቃድ የመስጠት እና MCPS ንብረት ላይ ድሮኖችን ማብረር ለሚፈልጉ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች መመሪያ የመስጠት ሃላፊነት አለበት።

2. በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ንብረት ክልል ላይ ለስራ አገልግሎት (ለምሳሌ፡- የግንባታ ሥራን ወይም የአውቶቡስ መናኸሪያዎችን ለመቆጣጠር) የድሮን በረራዎች ከመደረጋቸው በፊት፤ ለስርዓተ-አቀፍ የደህንነት እና የአስቸኳይ ጊዜ አስተዳደር (OSSEM) ስርአት አቀፍ የደህንነት ቡድን መሪ እና ለፋይናንስ አገልግሎት ክፍል የአደጋ ስጋት አስተዳደር ባለሙያ ማሳወቅ አለባቸው።

3. በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ገንዘብ ሰው አልባ ድሮን መግዛት ወይም የድሮን ልገሳ መቀበል አይመከርም። ሰው አልባ ድሮኖችን በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ገንዘብ የገዙ ወይም በስጦታ ያገኙ ማናቸውም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የሥራ ክፍሎች/ዲፓርትመንቶች ከ– ጋር ማማከር አለባቸው፡-

   a) MCPS ደንብ EGF-RB ጋር ይጣጣም እንደሆን ለማረጋገጥ MCPS የቪዲዮ ሪከርዶች ጥበቃ እና ይፋ ስለማድረግOSSEM የቪዲዮ ሪኮርዶች ባለሙያ፣ እና

   b) የፋይናንስ አገልግሎት ክፍል የአደጋ ስጋት ማኔጅመንት ባለሙያ።

   c) እንዲሁም MCPS ደንብ DJA-RB፣በባጀት ያልተያዘ ገንዘብ በመጠቀም የቁሳቁስ እና መሳሪያዎች ግዢ እና በልግስና የተሰጡ እቃዎችን መቀበል የሚለውን ይመልከቱ።

B. ድሮን ኦፐሬተር እና የድሮን በረራ እቅድ ማጽደቅ

1. የድሮን ኦፐሬተር ማመልከቻ

   ወቅታዊ FAA የሪሞት ፓይለት ሰርተፍኬት ያለው/ያላት ግለሰብ በድሮን ኦፐሬተርነት እንደሚከተለው ሊፈቀድለ(ላ)ት ይችላል።

   (1) MCPS ቅጽ 360-26፣ MCPS የድሮን ኦፕሬተር ማመልከቻይሙሉ።

   (2) ለአመልካቹ ከ FAA-የተሰጠ ወቅታዊ የሪሞት አብራሪ ሰርተፍኬት ቅጂ አያይዘው ያቅርቡ።

   (3) የጣቢያውን አስተዳዳሪ ፈቃድ ለማግኘት እና ሁሉንም ቅጾች OCIP ፋውንዴሽን ጽ/ቤት የማቅረብ ኃላፊነት ላለው የጣቢያው ስፖንሰር ቅጽ 360-26 ያቅርቡ።

   (4) ቅጽ 360-26 እና ቅጽ 360-32፣ MCPS የድሮን በረራ እቅድ ማመልከቻበተመሳሳይ ጊዜ ማቅረብ ይቻላል።

2. ለድሮን የበረራ እቅድ ፍቃድ መስጠት

   a) ለተወሰኑ ቀናት ወይም ቀጣይ ተከታታይ ቀኖች የድሮን በረራ ለማድረግ ወይም ተከታታይ በረራዎችን ሊፈቅዱ ይችላሉ፣ (ለምሳሌ፡- እንደሚከተለው በመካሄድ ላይ ለሚገኝ የሥርዓተ ትምህርት ተደጋጋሚ በረራ)

(1) MCPS ቅጽ 360-32፣ MCPS የድሮን በረራ እቅድ ማመልከቻ ሞልተው ከታሰበው የበረራ ጊዜ ቢያንስ ከሁለት ሳምንት በፊት ወደ OCIP ፋውንዴሽንስ ቢሮ መቅረብ አለበት

(2) ቅጽ 360-32 የሚከተሉትን ማካተት አለበት –

(a) MCPS ቅጽ 360-26 ለታቀደው የሰው አልባ ድሮን ኦፐሬተር ከ FAA የተሰጠ የሪሞት ፓይለት ሰርተፍኬት (የድሮን ኦፐሬተሩ(ሯ) ከዚህ ቀደም በተመሳሳይ የትምህርት አመት ጥያቄው(ዋ) ተቀባይነት አግኝቶ ከሆነ የተፈቀደለ(ላ)ትን ቅጽ 360-26 እና ወቅታዊ FAA ሰርተፍኬት ተያይዞ መቅረብ አለበት)

(b) የበረራ እቅድ ካርታ

b) ቀጣይነት ያለው የበረራ እቅድ ፈቃድ የሚሰጠው ከአንድ አመት ላልበለጠ ጊዜ (ከጁላይ 1 እስከ ጁን 30) ነው።

c) የድሮን ኦፐሬተር እና/ወይም የጣቢያው ስፖንሰር በረራው የሚካሄድበትን ቦታ እና ሰዓት ከ OCIP ፋውንዴሽን ቢሮ የተረጋገጠ የበረራ እቅድ በፋይል ሊኖራቸው ይገባል።

C. በድሮን የሚፈጠሩ ክስተቶች እና ክስተቶቹን ሪፖርት ስለማድረግ

1. በድሮን በረራ ምክንያት የሚፈጠር ማንኛውንም ክስተት ወዲያውኑ ለጣቢያው አስተዳዳሪ ማሳወቅ ይገባል፣ የጣቢያው አስተዳዳሪ MCPS ደንብ COB-RA፣የተከሰተ አደጋን ሪፖርት ስለማድረግባለው ድንጋጌ መሠረት በአግባቡ ተግባራዊ ያደርጋል።

2. ቅጽ 360-33፣ MCPS በድሮን ምክንያት የተከሰተ አደጋ ቅጹ ተሞልቶ 24 ሰአታት ውስጥ ወደ OCIP ፋውንዴሽን ጽ/ቤት እና OSSEM ስርዓት አቀፍ የደህንነት ቡድን መሪ፣እና ቅጂው ለጣቢያው አስተዳዳሪ መቅረብ አለበት።

3. ከጣቢያው አስተዳዳሪ፣ OCIP/ተወካይ፣ ወይም OSSEM/ተወካይ ጋር በመመካከር ፍቃድ የተሰጣቸው የበረራ እቅዶች በማንኛውም ጊዜ ሊሻሩ ይችላሉ፣ እና በድሮን አደጋ ምክንያት ሌላ የፕሮግራም ማስተካከያዎች ሊተገበሩ ይችላሉ።

4. ሰው አልባ ድሮኑ በማንኛውም ሰው ላይ ከባድ ጉዳት ካደረሰ ወይም የትኛውንም ህሊናን የሚያስት ጉዳት ካደረሰ ወይም በማንኛውም ንብረት ላይ ጉዳት ካደረሰ (ከድሮኑ በስተቀር) እና ጉዳት የደረሰበትን ንብረት ለመጠገን ወይም ለመተካት $500 ዶላር በላይ (የትኛውንም ዝቅተኛ ሂሳብ) የሚፈጅ ከሆነ የደረሰው አደጋና የጉዳት መጠን ከ 10 ቀን ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ድሮኑን የሚቆጣጠረው FAA ሪሞት ፓይለቱ ወደ FAA ሪፖርት ማድረግ እንደሚጠበቅበት ይደነግጋል።) ለ MCPS ዓላማ፥ የጣቢያው ስፖንሰር እና የጣቢያው አስተዳዳሪ ሪፖርቱ በወቅቱ መቅረቡን ለማረጋገጥ ከድሮን ኦፐሬተሩ(ሯ) ጋር ማስተባበር አለባቸው።

D. ሪከርድ መያዝ

1. OCIP ፋውንዴሽን ጽህፈት ቤት ዝርዝር ሁኔታውን መዝግቦ የመያዝ ሃላፊነት አለበት–

   a) ወቅታዊ የሪሞት ፓይለትነት FAA ሰርተፊኬት ያላቸው እና ለትምህርት ዓላማ MCPS ለድሮን ኦፕሬተርነት ፈቃድ የተሰጣቸው የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች፣

   b) የተፈቀደ የድሮን በረራ ዕቅዶች፣ እና

   c) ሪፖርት የተደረጉ የድሮን አደጋ ክስተቶች።

2. የጣቢያው አስተዳዳሪ በጣቢያው ላይ ለሚደረጉ የድሮን በረራዎች በሙሉ ሪከርድ መያዝ አለበ(ባ)ት። OCIP ፋውንዴሽን ቢሮ የናሙና ማስታወሻ ደብተር/log ይዘጋጃል። የድሮን በረራ ማስታወሻ ደብተር/log –

   a) የተፈቀደ የበረራ እቅድ እና የተፈቀደ የፀደቁ ቅጾችን እና ማንኛውንም ሪፖርት የተደረጉ ክስተቶችን ማካተት አለበት፣ እና

   b) በተጠየቀ ጊዜ ሁሉ ወደ OCIP ወይም OSSEM ማቅረብ አለበት።

**ተዛማጅ ሠነዶች፦** 49 USC 44809፡ ለተወሰነ የመዝናኛ ተግባር በልዩ ሁኔታ የሚፈቀድ ሰው አልባ አውሮፕላን፤14 CFR ክፍል 107 የአነስተኛ ሰው አልባ አውሮፕላን ሲስተሞች፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የማህበረሰብ አገልግሎት ክፍል የህዝብ መገልገያዎች ቢሮ (CUPF) የፋሲሊቲ አጠቃቀም ፍቃድና ስምምነት

**ስለ ደንቡ ታሪክ፦** አዲስ ደንብ ፀድቆ በሥራ ላይ የዋለው ጁን 5, 2024 ነው።

# የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የፀረ-መድሎአዊነት መግለጫ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በዘር ሐረግ፣ በጎሣ፣ በቀለም፣ በትውልድ ሐረግ፣ በዜግነት፣ በሃይማኖት፣ በስደት ሁኔታ፣ በጾታ፣ በጾታ መገለጫ፣ በጾታ ማንነት፣በጾታዊ ዝንባሌ፣በቤተሰብ መዋቅር/የወላጅነት ሁኔታ፣ በትዳር ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ሕገወጥ አድልዎ ማድረግን ይከለክላል። ዕድሜ፣ ችሎታ (ግንዛቤ፣ ማህበራዊ/ስሜታዊ እና አካላዊ)፣ ድህነት እና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ ቋንቋ፣ ወይም ሌላ በህግ ወይም ህገ-መንግሥታዊ ጥበቃ የተደረገላቸው ባህሪያት ላይ የሚደረግ ማናቸውንም ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። መድሎ ወይም አድሎአዊነት፤ ሕብረተሰባችን ለረዥም ጊዜ እኩልነት፣ ፍትኃዊነት፣ አብሮነት፣ ሁሉን አቀፍነትን፣ ለማስፈን እና ለማዳበር/ለመንከባከብ ሲካሄድ የቆየውን ጥረት ይሸረሽራል/ያበላሻል። ቦርዱ ጥላቻን የሚያራምድ ቋንቋን እና/ወይም ምስሎችን እንዲሁም ምልክቶችን መጠቀምን ይከለክላል፥ በተለይም በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ሥራ ወይም እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ማደናቀፍ ሊያስከትል የሚችል ድርጊት-እንቅስቃሴ የተከለከለ ነው። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የሞንትጎመሪ ካውንቲ "የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ ACA" ይመልከቱ፡- "ከአድሎአዊነት ነጻ የሆነ ፍትሃዊነት፥ ሚዛናዊነት፥ እና የዳበረ ባህል"። ይህ መመርያ እያንዳንዱ ተማሪ ትኩረት የሚሻ መሆኑ(ኗ)ን  እና በተለይም የትምህርት ውጤቶች በምንም አይነት በግለሰብ ትክክለኛ ወይም ይሆናል ተብሎ በሚገመት ግላዊ ባህርያት የሚተነበይ እንደማይሆን የቦርዱን እምነት ያረጋግጣል። ፖሊሲው በተጨማሪም ፍትህ/እኩልነትን/ሚዛናዊነትን የሚያዛቡ ነገሮችን ለይቶ በማወቅ በቅድሚያ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎችን፥ የተዛባ ስውር አመለካከትን፣ ጭፍን/መሠረተ-ቢስ ልዩነት ማድረግን፣ በተቋማት የሚፈጸሙ መዋቅራዊ መሰናክሎችን፣ በትምህርት እና በሥራ ላይ እኩልነት እንዳይኖር ተፅእኖ የሚያደርጉ አሠራሮችን የሚገታ/የሚፃረር መሆኑን ያስገነዝባል። MCPS ለወንድ/ለሴት ልጆች በስካውትነት እና በሌሎች የወጣት ቡድኖች ለመመደብ እኩል ተደራሽነት ይሰጣል።

A. በሜሪላንድ ስቴት ፖሊሲ መሠረት ሁሉም የህዝብ እና በህዝብ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ትምህርት ቤቶች እና የትምህርት ቤት ፕሮግራሞች የሚከተሉትን ድንጋጌዎች በማክበር መንቀሳቀስ አለባቸው፡-
   (1) 1964 የፌደራል ሲቪል መብቶች ህግ አንቀጽ VI፣ እና
   (2) በሜሪላንድ ኮድ የትምህርት ደንብ አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ 7፣ ይኼውም የህዝብ እና በህዝብ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ትምህርት ቤቶች እና ፕሮግራሞች፡-
      (a) በዘር፣ በጎሳ፣ በቀለም፣ በሃይማኖት፣ በጾታ፣ በእድሜ፣ በብሔር፣ በጋብቻ ሁኔታ፣ በፆታዊ ሁኔታ፣ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት፣ ወይም የአካል ጉዳተኝነት ምክንያት፣ አሁን ባሉት ተማሪዎች ላይ፣ የወደፊት ተማሪዎች ላይ፣ ወይም የአሁን ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ላይ አድልዎ ማድረግ የተከለከለ ነው፣
      (b) በአንድ ግለሰብ ዘር፣ ጎሳ፣ ቀለም፣ ምክንያት የወደፊት ተማሪዎችን መመዝገብ እምቢ ማለት፣ የአሁኑን ተማሪዎች ማባረር፣ ወይም ከአሁን ተማሪዎች፣ የወደፊት ተማሪዎች ወይም የአሁኑ ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆችን ወይም አሳዳጊዎችን የሃይማኖት፣ የጾታ፣ የዕድሜ፣ የብሔር፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የፆታ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት ወይም የአካል ጉዳት፣ የመሳሰሉትን ምክንያት በማድረግ መብቶችን መከልከል፣ ወይም
      (c) የትምህርት ውጤቱ(ቷ) ምንም ይሁን ምን መርሃ ግብሩ ወይም ትምህርት ቤቱ በተማሪው(ዋ) ላይ አድሎአዊነትን ፈጽመዋል የሚል ቅሬታ ባቀረበ(ች) ተማሪ ወይም ወላጅ ወይም አሳዳጊ ላይ ቅጣት ማድረግ፣ ወይም ማንኛውንም ሌላ የበቀል እርምጃ መውሰድ የተከለከለ ነው**

እባክዎን የግንኙነት መረጃ እና የፌዴራል፣ የስቴት፣ ወይም የአካባቢ መረጃ ይዘትን በተመለከተ መስፈርቶቹ በዚህ ሰነድ እትም ላይ ተለውጠው ሊሆን ይችላል፥እና በወቅታዊ መረጃ እንደተተካ ልብ ይበሉ።  በዚህ ውስጥ የተካተቱትን መግለጫዎች እና ማመሳከሪያዎችን ወቅታዊ መረጃ ለማግኘት እባክዎን ይህንን በይነመረብ ይመልከቱ፡- www.montgomeryschoolsmd.org/info/nondiscrimination

<table>
<tr><td>በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች ላይ አድልዎ ሲፈጸም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-***</td><td>በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች ላይ ስለሚደርስ መድልዎ ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-***</td></tr>
<tr><td>Director of Student Welfare and Compliance<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>15 West Gude Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 | SWC@mcpsmd.org</td><td>Human Resource Compliance Officer<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 | DCI@mcpsmd.org</td></tr>
<tr><td>1973 የተሃድሶ ድጋንብ ሰክሽን 504 መሠረት ለተማሪ የመገልገያ/አኮሞዴሽን/ጥያቄ ማቅረቢያ አድራሻ ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-</td><td>በአካል ጉዳተኛ አሜሪካውያን ህግ መሠረት ለሰራተኞች የመገልገያ/የአኮሞዴሽን/ጥያቄ ማቅረቢያ አድራሻ ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-</td></tr>
<tr><td>Section 504 Coordinator<br>Office of School Support and Improvement<br>Well-Being and Student Services<br>850 Hungerford Drive, Room 257, Rockville, MD 20850<br>240-740-3109 | 504@mcpsmd.org</td><td>ADA Compliance Coordinator<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 | DCI@mcpsmd.org</td></tr>
<tr><td colspan="2">ታይትል IX ስር ስለ ፆታዊ መድልዎ፣ ጾታዊ ትንኮሳን ጨምሮ፣ በተማሪዎች ላይ ወይም በሰራተኞች ላይ ስለሚደረግ ጥቃት ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-***</td></tr>
<tr><td colspan="2">Title IX Coordinator<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>15 West Gude Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 | TitleIX@mcpsmd.org</td></tr>
</table>

*ይህ መግለጫ ከተሻሻለው የፌዴራል የአንደኛ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ህግ ጋር የተሣለጠ ነው።
**ይህ መግለጫ የሜሪላንድ ዝርዝር ደንብ/ኮድ አንቀጽ 13A.01.07. ጋር የተሣለጠ ነው።
***የመድሎአዊነት ቅሬታዎችን ለሚከተሉት ሌሎች ኤጀንሲዎችም ማቅረብ ይቻላል፡-
U.S. Equal Employment Opportunity Commission (EEOC), Baltimore Field Office, GH Fallon Federal Building, 31 Hopkins Plaza, Suite 1432, Baltimore, MD 21201, 1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY);  Maryland Commission on Civil Rights (MCCR), William Donald Schaefer Tower, 6 Saint Paul Street, Suite 900, Baltimore, MD 21202, 410-767-8600, 1-800-637-6247, mccr@maryland.gov; Agency Equity Officer, Office of Equity Assurance and Compliance, Office of the Deputy State Superintendent of Operations, Maryland State Department of Education, 200 West Baltimore Street, Baltimore, MD 21201-2595, oeac.msde@maryland.gov; or U.S. Department of Education, Office for Civil Rights (OCR), The Wanamaker Building, 100 Penn Square East, Suite 515, Philadelphia, PA 19107, 1-800-421-3481, 1-800-877-8339 (TDD), OCR@ed.gov, ወይም www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

ይህንን ሠነድ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ በተጨማሪ በአማራጭ ቋንቋ/ፎርማት ማግኘት ካስፈለገ "Americans with Disabilities Act" ድንጋጌ መሠረት MCPS Office of Communications በስልክ ቁጥር፡- 240-740-2837፣ 1-800-735-2258 (Maryland Relay) ወይም PIO@mcpsmd.org በመጠየቅ ማግኘት ይቻላል። የምልክት ቋንቋ ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ግለሰቦች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የትርጉም አገልግሎት ጽ/ቤትን በዚህ ኤሜይል ወይም በስልክ መጠየቅ ይችላሉ። MCPS Office of Interpreting Services ስልክ ቁጥር 240-740-1800, 301-637-2958 (VP) mcpsinterpretingservices@mcpsmd.org, ዐወይም MCPSInterpretingServices@mcpsmd.org

ሀምሌ 2024